አፍሪካ ቲቪ

8

# ሁሉም ሙስሊም ማወቅ ያለበት “የልብ ተግባራት” 3

በቴሌግራም

አፍሪካ አካዳሚ

AFRICA ACADEMY

AAcademyEthio

www.AfricaAcademy.com

አፍሪካ ዲናዊ እውቀት አካዳሚ

(ሁሉም ሙስሊም ማወቅ ያለበት "የልብ ተግባራት")

አፍሪካ አካዳሚ

# ማመስገን እና መታገስ

ሙስሊምና ሌሎችም በዘገቡት ከሱሐይብ በተወራዉ ሐዲስ ረሱል ﷺ እንዲህ ይላሉ፡-

"የሙዕሚን ነገር ይገርማል፤ የሙዕሚን ሁሉ ነገሩ መልካም ነው ይህ ለማንም አይሆንም ለሙዕሚን እንጂ። መልካም ነገር ከገጠመው አላህን ያመሰግናል በዚህም መልካም ይሆንለታል። አስቸጋሪ ነገር ቢገጥመው ይታገሳል ይህም መልካም ይሆንለታል።"

8

AAcademyEthio

www.AfricaAcademy.com

- **ሽኩር (ምስጋና)፡-**ነብዩ ﷺ አህመድ በዘገቡት ሐዲስ ‹‹በልቶ የሚያመሰግን ፆም እንደሚታገስ ነው፡፡>> ብለዋል፡፡

- ልቦና ውስጥ ከእምነትህ ማመስገን ማለት የአላህ ውለታ በሰዎች ምላስ ላይ በማመስገንና በአካላቸው ላይ በአምልኮ ሲገለፁ መታየቱ ነው፡፡ እናም ምስጋና በልብ፤ ምላስና በአካል የሚገልፅ ከፍተኛ ተግባር ነው፡፡



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

- **ትዕግስት (ሰብር)፡-** ትዕግስት ማለት የደረሰበትን ችግር ከአላህ ሌላ ለማንም አካል ስሞታን አለማቅረብ ነው፡፡
  - ‹‹ ታጋሾች መንዳቸውን የሚሰጡት ያለግምት ነው›› ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ ‹‹ለመታገስ የተጣጣረ አላህ ትግስት ይሰጠዋል፡፡ ማንም ሰው ከትግስት የበለጠና የሰፋ የተሰጠ የለም፡፡ ››
  - ዑመር ረ.ዐ እንዲህ ብለዋል፡- "በምንም ነገር ስፈተን አላህ አራት ፀጋዎችን ይሰጠኛል፡፡ (1) በዱኒያ ላይ አለመሆኑ፤
    (2) በጣም የከበደና ከአቅም በላይ አለመሆኑ፤
    (3) አሚን ብየ እንድቀበል መደረጉ፡፡
    (4) ከአላህ ምንዳ ተስፋ እንዲደረግለት ማድረጉ ነው፡፡"



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

አፍሪካ አካዳሚ

ትዕግስት ብዙ ደረጃ አለው፡፡

- **ዝቅተኛው** እሱም የደረሰውን እየጠሉ ስሞታን መተው ነው፡፡
- **መካከለኛው** ደግሞ የደረሰበትን ነገር አሚን ብሎ ተቀብሎ አለማስሞት ነው፡፡
- **ከፍተኛው** የትዕግስት ክፍል በደረሰበት ችግር ላይ ከማስሞት ይልቅ አልሐምዱሊላህ ብሎ አላህን ማመስገን ነው፡፡ ተበድሎ በበዳዩ ላይ ዱዓ ያደረገበት ሰው በራሱ ስለተበቀለ ታገሰ አይባልም፡፡



www.AfricaAcademy.com
AAcademyEthio

አፍሪካ አካዳሚ

- **ትዕግስት ሁለት ዓይነት ነው፡፡**

1. አካላዊ ትዕግስት ሲሆን እዚህ ላይ ስለዚህ ክፍል በሰፊው ማውሳት አንፈልግም
2. ስሜትንና የግል ፍላጎትን በማሸነፍ የሚደረገው መንፈሳዊ ትግስትን ነው፡፡

- የሰው ልጅ በዚህ ዓለም ኑሮው ውስጥ የሚያጋጥሙት ችግሮች ከሁለቱ አንዱ ነው፡፡
- ሀ) ስሜቱን የሚስማማ ሲሆን ይህን ለመወጣት የአላህን ሐቅ ጠብቆ፤ አላህን አመስግኖ፤ ከእሱ ትእዛዝ ውጪ እንዳይሆን ተጠንቅቆ ለመፈፀም መታገስ ሲሆን ክፍሉ ግን ግዴታው የግዴታዎቹን ለመወጣት የሚያስችለውን ያህል ነው፡፡



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

አፍሪካ አካዳሚ

• ለ) ከስሜት ጋር የሚጣረስ ሲሆን ይህም ለሶስት ይከፈላል፡፡

1. በአላህ ኢባዳ ላይ የሚደረገው ትዕግስት ሲሆን ከዚህ ክፍሉ ግዴታው የግዴታዎቹን መወጣት የሚያስችለውን ያህል ነው፡፡ የሚወደደው ደግሞ እኒህ ውሳኔዎች ላይ የሚወዱትን ለመተግበር የሚያስችለው የትግዕስትን ክፍል ነው፡፡

2. አላህ ከከለከላቸው ነገሮች መታገስ ነው ከዚህም ክፍል ግዴታ የሚሆነው የተከለከሉትን መተው ሲሆን የሚወደደው የሚጠሉትን መተው ነው፡፡



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

አፍሪካ አካዳሚ

**3.** በአላህ ውሳኔዎች ላይ የሚደረገው ትግዕስት ነው፡፡ ከዚህም ክፍል ግዴታው ምላስን ከማማረር መቆጠብንና ልቦናን ከመቃወምና ከመጥላት መከልከልና አካላትን ደግሞ አላህ የማይወዳቸውን ሙሾ ማልቀስ አንገትዩን መቅደድና ደረትን መምታት ከመሳሰሉት ነገሮች ሁሉ መቆጠብ ነው፡፡ ከዚህ ክፍል የሚወደደው የአላህን ውሳኔ በልቡ አሚን ብሎ መቀበል ነው፡፡



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com